EthioLion

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 3/2002

## በምርጫ ዝግጅት ሳቢያ ወያኔ የሕዝብን መብት ረገጣ አባብሷል!

ወያኔ ሽር ጉድ የሚልለት ህዝቡ ግን አይመለከተንም ባለው ምርጫ በግድ ለማሳተፍና ሽፋን ለማግኘት ሲል ወያኔ በሕዝብ ላይ ልዩ ልዩ ጫናን እያደረገና መብት እየረገጠ ነው:: በቅርቡ በአዲስ አበባ የወያኔ ፖሊሶችና ካድሬዎች ከቤት ቤት እየሄዱ ለምርጫ የተመዘገባችሁ መሆኑን መረጃ አሳዩን/ካርድ አሳዩን እያሉ በማስጨነቅ ላይ መሆናቸው ተዘግቧል:: የተመዝጋቢው ቁጥር በማነሱ ወያኔ ተመዘገቡ በሚል የተጋነነ ቁጥር በመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨትም ግድ ሆኖበታል:: ሕዝቡ በ1997 የደረሰበትን አልረሳምና በመጪው የወያኔ የምርጫ ጋጋታ ላለመሳተፍ መወሰኑና አብዛኛውም አልመዘገብም ማለቱ የሚታወቅ ነው::

የወያኔ ቡድን ከሥራ ትታገዳላችሁ፤ ለተራባችሁ ምግብ አይሰጣችሁም፤ የንግድ ፍቃድ ትቀማላችሁ፤ ...ወዘተ በሚል በግድ የኢሕአዴግ አባል በማድረግ ስድስት ሚሊዮን የሚጠጉ አባሎች አሉኝ የሚል ሲሆን መጪውን ምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመሰየም ዝግጅቱን ሁሉ ጨርሶና የ1997ኡ እንዳይደገመበት ሴራውን ሁሉ ተብትቦ እንደሚገኝ የአደባባይ ምስጢር ነው:: አፋኞቹንም ለዚያን ወቅት ያዘጋጀ ሲሆን ከወዲሁም የሌሎች ድርጅቶችን አባላት እያሰረና እያሰቃየ መሆኑን --ምንም እንኳን የሥነ ሥርዓት ህግ ቢፈርሙም - ድርጅቶቹ ራሳቸው አጋልጠዋል:: በግድ ተመዝገቡ፤ እኛን ካልመረጣችሁ ዋ! ማለቱ መብዛቱ ወያኔና ምርጫው በሕዝብ ዘንድ የከሰረ ፖለቲካ ተደርገው መወሰዳቸውን የሚያረጋግጥ ነው:: በሰሞኑ በአዲስ አበባ በተከተል አለቃህን መንፈስ የብአዴንም ካድሬዎች አማራ በሚሏቸው ቤተሰቦች ዘንድ በር እያንኳኩ የአማራ ልማት ድርጅትና አልፎም የብአዴን አባል ሁኑ በማለት ግፊት መጀመራቸውም ታውቋል:: ከዚህ እስከ ግንቦት በሕዝብ ላይ የሚደረገው ጫናና ግፊት፤ የሚደርሰውም እንግልትና መብት ረገጣ እየጨመረ እንጂ እያነሰ አይመጣም ቢባል ስህተት አይደለም::

የወያኔ ዘረኛ ቡድን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከሚያካሂደው የዕብሪት ቀልድ አንዱ በየጊዜው ምርጫ ብሎ የሚወራጭበት ሂደት ነው:: በኢትዮጵያ መቸም ቢሆን መች ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ ሲካሄድ ያላየው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ በ1997 በወያኔ ድምፁን ተሰርቆና ፍጅትም ደርሶበት --እስከዛሬም በዚያን ጊዜ የታሰሩት ሺዎች አልተፈቱምናም -- ዳግም በግንቦት ሊታለልና መቀለጃ ሊሆን ከቶም ዝግጁ አይደለም:: መጪው ምርጫ በወያኔ ሽንፈት ይጠናቀቃል ወይም ፍትሃዊ ሊሆን ይችላል የሚል ቅዠትም የሕዝብ አይደለም:: በመሆኑም የወያኔ ማስገደጃዎችና ማስፈራሪያዎች የመጪው ምርጫን ዋጋ ቢስነት ሆነ የወያኔን አረመኔ አምባገነንነት ቅንጣትም ሊሸፍን ሆነ ሊለውጥ የሚችል አይደለም::

ኢሕአፓ ፀረ ኢትዮጵያውን የወያኔ አገዛዝ ለመጣል ትግላችንን እናፋፍም ይላል!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

Ethiopia will prevail !